# ለአደጋ ጊዜ የሚሆን ውኃ ማስቀመጥ

**የተፈጥሮ አደጋ እንደ የመሬት መንቀጥቀጥ በሚከሰትበት ጊዜ፣ የውኃ ቧንቧዎች ሊሰበሩ ይችላሉ። ስለዚህ ለያንዳንዱ የቤተሰብዎ አባል ቢያንስ ለ3 ቀን የሚሆን ውኃ ማስቀመጥ አለብዎት።**

## ለአደጋ ጊዜ የሚሆን ውኃ እንዴት ማስቀመጥ ይቻላል

ለአደጋ ጊዜ የሚሆን ውኃ ለማስቀመጥ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ደረጃዎች ከተከተሉ፣ ባለ 2 ሊትር ጠርሙዞች በጣም ጠቃሚ፣ ውኃ ማጠራቀሚያ ሊሆኑ ይችላሉ።

- መያጃው ንጹህ መሆኑን ያረጋግጡ። የሻይ ማንኪያ 1/8 የሚያህል በረኪና እና 2 ሲኒ ውኃ በመያዣው ውስጥ በማስገባት፣ መያዣውን ከድነው በማዋዛወዝ ይጠቡት። በመክደኛው አከባቢ እና እላይ ያለው ክፍል በሙሉ በደምብ ይጠቡት

- መያዣውን ባዶ በማድረግ ብጹህ ውኃ እስከ ላይ ይምሉት። በደምብ ያሽጉት እና፣ ለአደጋ ጊዜ የሚሆን ውኃ የሚል ጽሑፍ መያዣው ላይ ያኑሩ። ከዛም ውኃው የተሞላበት ቀን እዛ ላይ ይጻፉት።

- በተቻለ መጠን ብዙ ውኃ ያስቀምጡ! በቤተሰብዎ ውስጥ የሚኖረው ለያንዳንዱ ሰው **ስድስት ባለ 2 ሊትር ጠርሙዞች** ውኃ ማስቀመጥ አለብዎት።

- ሁል ጊዜ በየ 6 ወር መያዣውን ባዶ በማድረግ፣ እንደገና ንጹህ ውኃ ይምሉት። (በበጋ እና በጸደይ ወቅቶች ሰዓቱን በሚቀይሩበት ጊዜ፣ የውኃ መያዣዎቹን ባዶ በማድረግ እንደገና የሚሞሉበት ጥሩ ጊዜ ነው።)

ማስጠንቀቂያ፥ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ነገሮች መጠቀም የለብዎትም፤ **ከመስተዋት የተሰራ ጠርሙዝ** (በቀላሉ ስለሚሰበር)፣ **ፕላስቲክ የወተት መያዣ** (ለመክደን ከባድ ስለሚሆን እና በቀላሉ ይቀደዳል)፣ ወይም ደግሞ **በረኪና ወይም ለጤና አደገኛ የሆኑ ኬሚካሎች መያዣ የነበረ።**



Amharic